# የACPS Express 10/21/2022: በኦፒኦይድ አደጋ (Opioid Crisis) ላይ፣ ከጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) የተሰጠ የቪዲዮ መልዕክት

## በኦፒኦይድ አደጋ (Opioid Crisis) ላይ፣ ከጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) የተሰጠ የቪዲዮ መልዕክት




ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ ባጋሩት፣ የቪዲዮ (video) መልዕክትን የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ቤተሰቦችን - ከተማሪዎቻቸው ጋር ስለ ኦፒኦይድ አደጋ (opioid crisis) በማነጋገር፣ እርዳታቸውን እና አጋርነታቸውን በመጠየቅ-አጋርተዋል። የACPS ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች፤ ለተማሪዎች የተዘጋጀውን - ተመሣሣይ የሆነውን ቪዲዮ - ሮብ፣ ኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 እንዲመለከቱ የሚደረግ፣ እና ከዶ/ር ኬይ-ዋየት (Dr. Kay-Wyatt) በቀጥታ-እንዲሰሙት ይደረጋል።

**አሌክሳንድርያ እና ACPS: የኦፒኦይድ ወረርሽኝ (Opioid Epidemic)ን ለመዋጋት፤ የመረጃ ምንጮችን ማጋራት**
ስለ ኦፒኦይድ አደጋ (opioid crisis) - በሁሉም-የሕይወት እና የስራ ተሞክሮ ውስጥ የሚገኙ በሃገሪቱ የማህበረሰቡ ዙሪያ-ውስጥ - የአሌክሳንድርያ ከተማን ጨምሮ፣ በትምህርት ቤት ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣቶች ላይ ተጽዕኖ ማድረሱ እየጨመረ መምጣቱን፤ በዜና አውታር ላይ በርካታ ሰዎች የሰሙት ሊሆን ይችላል። ነገር-ግን ኦፒኦይድስ (opioids) ምንድናቸው፤ እንዴት ነው ሰዎች ሊያገኙዋቸው የሚችሉት፣ እና እናንተ እንደ ACPS ተማሪ - የቤተሰብ አባልነታችሁ ምን ማድረግ ትችላላችሁ?

ኦፒኦይድስ (opioids) - ሕመምን-ለመቀነስ ጥቅም-ላይ የሚውል፤ ከፍተኛ ሱስነት ያላቸው ዕፆች/መድኃኒቶች (drugs) ናቸው። በሕክምና-መድኃኒት ማዘዣዎች (prescriptions) ውስጥ እንደ - oxycodone, hydrocodone, morphine እና fentanyl ሆነው የሚካተቱ፣ እና ሕገ-ወጥ ኦፒኦይድ (illegal opioid)፣ heroin ያሉት እና፤ በተለያየ ቅርጾች—በታብሌትነት፣ በፈሳሽነት እና በዱቄትነት ይመጣሉ።

በአሌክሳንድርያ ውስጥ - በትምህርት ቤት-ዕድሜ ውስጥ ያሉ ታዳጊ-ወጣቶች፣ የተጠቀሙት “little blue pill” - ፐርኮሴት/Percocetን የተጠቀሙ-መስሏቸው - ካለመጠን-የወሰዱ (Overdoses) የሆኑበት ምክንያት፣ እነዚህ እንክብሎች በፈንተኖል (fentanyl) የተጠቀለሉ፣ አልባሌ-የሆኑ እና ገዳይ-ነገሮችን ተከተው የያዙ በመሆናቸው - ከሞርፊን (morphine) የበለጠ እስከ 100-ጊዜ የበለጠ-ኃይለኛ የሆኑ እና፣ ከሄሮይን (heroin) ደግሞ እስከ 50-ጊዜያት የበለጠ-ኃይለኛ ናቸው። እንክብሎቹ (pills)፤ በብዛት - በ‘tin foil’ ላይ የሚጨሱ ናቸው። እነዚህ ዕፆች በመንገድ ላይ የሚሸጡ እና፣ በማህበራዊ-ሚዲያ መድረኮች ላይም - ቲክቶክ (TikTok)ን ጨምሮ የሚተዋወቁ-ናቸው። በተጨማሪም፤ ፈንተኖል (fentanyl) - በሁሉም አደንዛዥ-ዕጾች ውስጥ - ማርዋና (marijuana)፣ የቬፕ እስክሪብቶዎች (vape pens)፣ ኮኬን (cocaine) እና ሄሮይን (heroin) ውስጥ ተጠቅለው-የገቡ ናቸው።

በACPS ውስጥ - የተማሪ አገልግሎቶች (Student Services) & ፍትሃዊ እኩልነት መምሪያ - የባለብዙ-ደረጃዎች የስርዓት እገዛ (Multi-Tiered System of Support (MTSS)ን በመጠቀም፤ በአደንዛዥ-ዕጽ ጥቅም ወይም አለአግባብ-አጠቃቀም ውስጥ የገቡ ተማሪዎችን - እገዛ-ሰጪ የትምህርት ቤት አካባቢን ለመፍጠር፤ በመቅረብ-ያነጋግራቸዋል። የበለጠ ለማወቅ እና የመረጃ-ምንጮችን ለማግኘት - ACPS Substance Abuse Prevention & Educational Intervention webpage ጎብኙ፤ እና የበፈተኖል (fentanyl) ለወጣት እና አዋቂዎች የሚሰጠውን 'fact sheets' - በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ፣ እና በአረብኛ ተካትቶም-ይገኛል።

ይህን ዓይነት ዕፅ አንድ-ግዜም እኳን መጠቀም፤ አንድ-ሰው ሊገድል እንደሚችል እባካችሁ ተገንዘቡ። ከኦፒኦድስ (opioids) ከመሞከር-እነርሱን ለመጠበቅ፤ ከታዳጊ-ወጣት ጋር ግንኙነት/communicate (በስፓኒሽ) ማድረጋችሁ በጣም-ወሳኝ ነገር ነው። እነዚህ፣ ስለ ዕፆች ለመነጋገር ጠቃሚ-ነጥቦች (tips) ሆነው ሊረዷችሁ ይችላሉ። ሊኖር የሚችል የዕፅ አጠቃቀም ምልክቶችን - በልጃችሁ ላይ ገና-በለጋነቱ ተመልከቱ እና እራሳችሁን መጠኑን-ያለፈ የዕፅ አጠቃቀም (drug overdose) ምልክቶችን መኖር-አለመኖሩን በመለየት እወቁ። የሕክምና-ሠራተኞች እስከሚደርሱላቸው ድረስ፤ የዕፅ ከመጠን-ያለፉ-ሁኔታዎች (drug overdoses)ን የሚያመጣውን ጉዳት ለማድከም የሚረዳውን — በአፍንጫ-ውስጥ የሚረጭ (nasal spray) የሆነውን free Narcanን አግኝታችሁ-ያዙ። ለሕይወት-አስጊ በሆኑ ሁኔታ ላይ ለሚገኝ-ሰው፤ ወዲያውኑ 9-1-1 መደወል። እባካችሁ፤ በሐኪም-የታዘዙ መድሃኒቶችን (prescriptions) የመድኀኒት መቆለፊያ ነፃ ሣጥኖች (free medical lock boxes) በመጠቀም ቆልፉ፤ እና ጊዜያቸው-ያለፈባቸውን ወይም የማያስፈልጉ መድኀኒቶችን በተገቢው ሁኔታ በከተማው-ዙሪያ በሚገኙ ቦታዎች ማስወገድ-አለባችሁ። እናንተ፣ ወይም እናንተ የምትንከባከቡት ሰው እርዳታ ካስፈለፈው፤ እባካችሁ በ703-746-3400 ደውሉ እና ከማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of Community and Human Services) ውስጥ ከሚገኝ-ሠራተኛ ጋር ተነጋገሩ።

በኦፒኦይድ አደጋ (opioid crisis) ላይ ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት- alexandriava.gov/Opioids ጎብኙ፤ እና የአሌክሳንድርያ ከተማ - እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ እና ጤናማ እና አዎንታዊ የሆነ የቤተሰብ የመረጃ ምንጮች (resources) የሆኑትን - Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandriaን ተመልከቱት።

## የኦክቶበር (October)' ተማሪን እና ሠራተኛን እውቅና-መስጠት




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) አስተማሪዎች እና ተማሪዎች፤ ያላቸውን-ጊዜ በዋነኛነት-እንዲቀመጡ ያደረጋቸውን ቦታ በኦክቶበር (October) ወር ውስጥ አግኝተዋል። ስኬታማነታቸውን በማክበራችን፤ ኩራት ይሠማናል።

**የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) - ዶ/ር ባይነም (Dr. Bynum)፣ በንባብ (Reading) ሽልማት-በማግኘት እውቅና-አግኟል።**



የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ከK-8 ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆኑት ዶ/ር ኢንግሪድ ባይነም (Dr. Ingrid Bynum) - ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠውን ‘Reading Is Fundamental of Northern Virginia (RIF of NOVA) "Literacy Luminary” ሽልማትን - ንባብን እና ስነጽሁፍን በማህበረሰቡ-ውስጥ እንዲስፋፋ ባሳዩት የላቀ-ደረጃ እና ቀጣይነት ያለው ትጋት - ሽልማቱን አግኝተዋል። የክብር-ሽልማቱ ለዶ/ር ባይነም (Dr. Bynum) የተሰጣቸው፣ በ‘RIF of NOVA Golden Gala’ ዝግጅት - በኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 ነበር።

ባይነም (Bynum) - ልጅ እያሉ፤ በአስከፊ ድህነት ውስጥ በሪችመንድ ቨርጂኒያ ውስጥ በሚኖሩበት ጊዜ  ከ‘RIF’ መጽሐፍ ማግኘታቸው፤ ሕይወታቸውን እንደቀየረው ይናገራሉ። ከዓመታት በኋላ፤ በርካታ የትምህርት ዲግሪዎችን እጃቸው አድርገው - በትምህርት - በላቀ-ደረጃ የትምህርታዊ አመራርነት ዶክትሬታቸውን ጨምሮ፤ በዚህ 2016 የACPS የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ-መምህር በመሆን በንባብ ያላቸውን የጋለ-ስሜት ማሳየታቸውን ቀጥለዋል።

“ንባብ ማለት-ሁሉም ነገር ማለት-ነው፣” ብለዋል ዶ/ር ባይነም (Dr. Bynum) በአጽንዖት። “ሁሉም-ሰው እንዲያነብ ሁልጊዜ የምነግርበት-ምክንያት ለዚህ ነው... ማንበብ-አለባችሁ፤ በጣም ጠቃሚ-ነገር ነው።”  እንደ ዶ/ር ባይነም (Dr. Bynum) በመቀጠር እንደሚያነሳሱት፤ በግምት ወደ 900 የፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry) ተማሪዎች፤ በማንበብ፣ በንባብ ውጤቶች (reading scores) - በትምህርት ቤት - በሚገርም-ሁኔታ ተሻሽሏል። ፓትሪክ ሄንሪ (Patrick Henry)፣ በ ‘RIF of NOVA’ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው ከ37 ትምህርት ቤቶች እና ቦታዎች፤ አንዱ-ነው።

**የጄምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) አስተማሪ - ሻረን ፎክስ (Sharon Phox)፣ የ2022 የዓመቱ ምርጥ ብሩህ-አመለካከት ያላቸው አስተማሪ (Optimist Teacher) ሆነው ተሸልመዋል**



የጄምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪ - ሻረን ፎክስ (Sharon Phox)፣ የመጀመሪያ ዓመታዊ የ2022 የዓመቱ ምርጥ ብሩህ-አመለካከት ያላቸው አስተማሪ (Optimist Teacher) ሆነው - ከአሌክሳንድርያ ብሩህ-አመለካከት ክለብ አግኝተዋል። ሦስተኛ ክፍል ውስጥ የሚያስተምሩት - ፎክስ (Phox)፤ በ‘The Optimist’s Club Charter’ ዝግጅት በተካሄደበት ባለፈው ወር ውስጥ፣ የሰርተፊኬት እና የሞኒተሪ ሽልማቶችን አግኝተዋል።

በጀምስ ኬ. ፖልክ (James K. Polk) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙት የስራ-ባልደረባቸው - ቢል ጉድሪች (Bill Goodrich) - ፎክስ (Phox)ን የእጩነት የመረጧቸው እና እንዴት ከፍተኛ ለተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ለማሳካት የሚያጋሩም መስክረዋል። "ሚስ ፎክስ (Ms. Phox) ሁልጊዜ - በስጋት-ላሉ ተማሪዎች ልዩ የሆኑ የሚያስፈልጓቸውን-ነገሮች ምላሽ-መስጫ ስልቶችን-ለማግኘት፤ ያሏቸውን ጠንካራ-ጎኖች በመፈለግ እና ዋጋ ያላቸው እንደሆነ እንዲሰማቸው በማድረግ እና የመማሪያ-ክፍሉ የሚያግዙ-ስልቶችን ይዘው ይገኛሉ፣" ብለዋል ጉድሪች (Goodrich)። "ባላቸው መልካምነት - ምክንያት ሁሉም-ሰው - የ"Sunshine Club" ዋና-መሪ እያለ መጥራት እንደጀመረ እና፣ እሳቸውም-ይህን ተቀብለውታል።"

በዝግጅቱ ላይ - ስድስት ሌሎች እጩዎች የክብር-እውቅናን ያገኙ የሚያካትተው:

- ካትሪን ዴቪድሰን (Katherine Davidson)፤ በሦስተኛ ክፍል - በዳግለስ ማክአርተር (Douglas MacArthur) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ኤፕሪል ፉሲሊየር (April Fusilier)፤ መዋዕለሕፃናት - ጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት
- አንድሪአ ሂውስተን (Andrea Houston)፤ አራተኛ ክፍል - በናኦሚ ኤል. ብሩክስ (Naomi L. Brooks) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ሴሲሊ ፒስ (Cecille Peace)፤ አምስተኛ ክፍል - በማውንት ቨርነን ኮሚውኒቲ (Mount Vernon Community) ትምህርት ቤት
- ሪካርዶ ፔሬዝ (Ricardo Perez)፤ አራተኛ ክፍል - በጆን አዳምስ (John Adams) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ኬሪን ዊሊያምስ (Karin Williams)፤ አምስተኛ ክፍል - በጆን አዳምስ (John Adams) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት

የአሌክሳንድርያ የ'Optimist Club' - የዓመቱ ምርጥ ብሩህ-አመለካከት ያላቸው ሽልማት - አስቸጋሪ-በሆኑ ጊዜያቶች ውስጥ ብሩህ-አመለካከታቸውን በማሳየት የቆዩ - በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ የሚገኙ አስተማሪዎችን ለማክበር - የተቋቋመ ነው። ይህ በስራ-ባልደረባ አጋሮች መካከል የእጩነት ምርጫን በማድረግ፣ ቢያንስ የአምስት ዓመት የአገልግሎት ጊዜ ያላቸውን - ከK-5 የክፍል-ውስጥ (homeroom) አስተማሪዎች - ከK-5 የክፍል-ውስጥ (homeroom) አስተማሪዎችን የሚመርጡበት ሲሆን፣ በውስጣቸው በተተከለው ብሩህ-አመለካከት ላይ ተመርኩዞ - ተማሪዎችን ለማስተማር፣ ውጤታማ-እንዲሆኑ እና በተቻለ-መጠን በደንብ-ሊያከናውኑ ወደ-ሚችሉበት እንዲደርሱ ፍላጎት ያላቸው ናቸው።

**የእጅ-ኳስ ተጫዋች (Volleyball Player) ኮል ዊልሞንት (Chloe Wilmot) - የእጅ-ኳስ (Volleyball) ታሪክን - በACHS ውስጥ፣ ውጤታማ-ሆናለች**



የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የእጅ-ኳስ (volleyball) ተጫዋች ኮል ዊልሞንት (Chloe Wilmot) - 2,000 የስራ-ዘርፍ እገዛን - በሴፕቴምበር (Sept.) 17 ቀን 2022 ላይ ውጤታማ-ሆና ያገኘች ሲሆን፤ የትምህርት ቤት ሬከርድን በማግኘት - በእጅ-ኳስ ታሪክ ላይ እንዲቀመጥ አድርጋለች። የACHS ስሜት - በእጅ-ኳስ (volleyball) ቡድኑ የመጀመሪያ-አጀማመር ላይ - ከፍሬሽማን (freshman) አመቷ ጀምሮ እና ከ2,038 በላይ አሲስትስ

(assists) አግኝታ-አስደሳች ነበር። ከሁሉም ጊዜ የአሲስትስ (assists) ሬከርዷ በተጨማሪ፣ በ'aces' ከ188 ጋር የሁሉ-ጊዜ መሪ በመሆን እና በ 'digs' ደግሞ ከ587 ጋር በሦስተኛ-ደረጃ ላይ የምትገኝ፣ እና በብሎክስ (blocks) ከ61 ጋር በአምስተኛ ቁጥር-ላይ ነች። ዊልሞንት (Wilmot) - በተጨማሪም፤ በርካታ-ቁጥር ያላቸው ሽልማቶችን - የሚከተሉትን ጨምሮ አግኝታ-ነበር: የ2019 የሁለተኛ ቡድን የሁሉም ዲስትሪክት (Second Team All District)፣ የ2020 የመጀመሪያ ቡድን የሁሉም ዲስትሪክት (First Team All District)፣ የ2020 የሁለተኛ ቡድን የሁሉም ክልል (Second Team All Region)፣ የ2020 የቡድን የበለጠ ዋጋ-የሚሰጠው ተጫዋች (Team Most Valuable Player (MVP)፣ የ2021 የመጀመሪያ ቡድን የሁሉም ዲስትሪክት (First Team All District)፣ የ2021 የዲስትሪክት የሁሉም ቶርናመንት ቡድን (District All Tournament Team)፣ የ2021 የመጀመሪያ ቡድን የሁሉም ክልል (First Team All Region)፣ የ2021 ክልላዊ የሁሉም ቶርናመንት ቡድን (Regional All Tournament team) እና የ2021 የመጀመሪያ ቡድን የሁሉም ስቴት (First Team All State) - አግኝታለች። ዊልሞንት (Wilmot) - በተጨማሪም፤ በACHS የቀለም-ትምህርት - በእያንዳንዱ ዓመት፣ የክብር-ሚና ያለው ሆኖ ቆይቷል። ባለፉት ሦስት ወቅቶች ውስጥ፣ ዊልሞንት (Wilmot) እና የቡድን-አባላቶቿ - ሦስት የዲስትሪክ ታይትሎችን፣ ሁለት የክልላዊ ታይትሎችን እና አንድ የስቴት ሻምፒዮናዎችን አሸንፈዋል። በሶፎሞር እና በጁኒየር ወቅቷ-ጊዜ ውስጥ፣ ቡድኑ የ54-1 ሬከርድ ያገኛ - ብቸኛ-የተሸነፈበት ጊዜ በግማሽ-ፍፃሚ የስቴት ሻምፒዮና ጊዜ ብቻን ነበር።

**የ'ACHS' ተማሪ - ካደትስ ራንክ (Cadets Rank) - በ'Army JROTC Raiders' ፕሮግራም ላይ፣ ከፍተኛ-ቦታ ያላቸው ከሦስቱ ውስጥ - ቦታ አግኝተዋል**



በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ፣ በ'Army JROTC Raiders' ፕሮግራም ውስጥ፣ ከፍተኛ-ደረጃ ያለውን ሦስት ቦታዎችን ያገኙ የአሌክሳንድሪያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) ተማሪዎች፤ የእንኳን-ደስ አላችሁ መልዕክት እየደረሳቸው ነው። አርባ ቡድኖች፤ ሁለት 'ካዴትስ/cadets'ን ከዲሲ፣ ሜሪላንድ፣ እና ቨርጅኒያ አካባቢ ካሉ ትምህርት ቤቶች የተውጣጡ - አድካሚ የሆነ የሙሉ-ቀን ዝግጅትን አጠናቅቀዋል። የሴንቸሪ (Century) ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - 'Raiders Stakes' ውድድር - በሳይክስቪል ሜሪላንድ (Sykesville, MD) ውስጥ ተካሂዶ - የ'cadets'ን የአዕምሮ እና የአካላዊ ጥንካሬን ፈትኗቸው-ነበር። ዝግጅቶቹ ያካተቱት፤ የ3K እስቅድድም፣ የመሰናክል ኮርስ (obstacle course)፣ የገመድ-ድልድይ (rope bridge) እና የ'fireman-carry' የሩጫ ውድድር - ተካተው-ነበር።

ሁለት-የ'cadet' ቡድኖች - ከACHS JROTC Raiders - በከፍተኛ-ሦስት ቦታዎች ላይ - ደረጃዎችን አግኝተው-ነበር:

- የመጀመሪያ ደረጃ-ቦታ: ማርኮ አልቫሬዝ (Marco Alvarez) እና ጊዲዮን ሳም ካባ (Gideon Sam Kabba)
- የሁለተኛ ደረጃ-ቦታ: ኢቫን ፒኒላ (Ivan Pinilla) እና አንድሬስ ሮጃስ (Andres Rojas)
- የሦስተኛ ደረጃ-ቦታ: ዊሊያም ሬያስ (William Reyes) እና ባህራማንድ መሐመድ (Bahramand Mohammad)
- ከፍተኛ-ደረጃ ያገኝ የሴቶች ቡድን: አሜና ሳፊ (Amena Safi) እና ኢቤሪ ቱሪኪኦስ (Ibeyry Turcios)

**የ'ACHS' ኦርኬስራ - በማህበረሰቦች - በትምህርት ቤቶች ብሄራዊ ኮንፈረንስ ላይ አቅርበዋል**




ትኩረት-በተሰጠበት - በኦክቶበር (Oct.) 19 ቀን 2022 ላይ፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High chool (ACHS) ኦርኬስራ - ስራውን በ'Communities in Schools national' ኮንፈረስ በግራንድ ሃያት (Grand Hyatt)፣ በዋሽንግተን (Washington, D.C. ውስጥ እንዲያቀርብ በመጋበዙ- ስራውን-አሳይቷል። ለአከባበሩ የ'ACHS Orchestra' ትተጨማሪ-አድርጎ፣ ለዋና ተናጋሪ ለነበሩት ለክብር-እመቤት ዶ/ር ጂል ባይደን (First Lady Dr. Jill Biden) እንደ-ማስተዋወቂያ-ቅንብሩን አቅርቦ ነበር።

## የመጨረሻ-ዕድል: ለዓመቱ ምርጥ ርዕሰ-መምህር እና አስተማሪ፣ ተሸላሚ እጩዎችን ለማቅረብ- የመጨረሻ ቀኑ ኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 ነው



ሰኞ፣ ኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 - የACPS ማህበረሰብ አባላቶች — ቤተሰቦችን፣ ተማሪዎችን፣ ሠራተኞች እና የአሌክሳንድርያ ነዋሪዎችን ጨምሮ — ለACPS ተሸላሚዎችን በ'The Washington Post' [የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ-መምህር እና አስተማሪ ሽልማት ውስጥ]() እንዲካፈሉ እጩዎች ለማድረግ፤ የመጨረሻ-ማብቂያ-ቀን ይሆናል። ይህ ፕሮግራም፤ በክልሉ ውስጥ፣ በትምህርት የላቀ-ደረጃን እውቅና-ይሰጣል። ከዚህ በታች-የተዘረዘረውን መስፈርት በመጠቀም- እጩዎችን እብካችሁ፤ አስገቡ:

- አስተማሪን ለእጩነት ለማቅረብ፤ ከኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 በፊት፣ ወደ ርዕሰ መምህሩ የጽሁፍ-መግለጫ ላኩ። እያንዳንዱ ርዕሰ መምህር - ከሠራተኞች ጋር ኢጋርነትን በመፍጠር፤ አንድ-እጩ - ከየትምህርት ቤቶቻቸው በመምረጥ ወደ ACPS የመጨረሻ ዙር እንዲያልፉ ያደርጋሉ።
- ርዕሰ መምህርን ለእጩነት ለማቅረብ፤ ወደ ሼሪ ቱሊአ (Sherri Tullia)፣ የመማር እና የአመራርነት መምሪያ (Department of Teaching, Learning and Leadership) ወደሆኑት፤ በsherri.tullia@acps.k12.va.us እስከ ኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 ድረስ፣ እባካችሁ መግለጫ ላኩ።

ለ'Washington Post' የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ ሽልማት፣ ብቁ ለመሆን፤ እጩ-የሚሆኑት የሙሉ-ሰዓት (full-time) አስተማሪ መሆን (ከቅድመ-መዋዕለሕፃናት እስከ 12ኛ)፤ እና እንደ ጋዜጣው ዝርዝር ግዛቶች መሠረት፤ እውቅናን-ካገኘ የዋሽንግተን ሜትሮ-

አካባቢ ክልልው ውስጥ ከሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆን አለባቸው። እጩዎቹ፤ እንደ አስተማሪነት ቢያንስ የ5 ዓመታት ልምድ ያላቸው፤ ከእነዚህም ዓመታት ውስጥ ሦስቱ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም አሁን በሚያገለግሉበት የትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ መሆን አለበት።

እጩዎቹ፤ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት በአስተማሪነት ማገልገል ያለባቸው እና የሚከተሉትንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

- በተማሪዎች ውስጥ የመማር እና ስኬታማ-የሆን ፍላጎትን መትከል የሚችሉ።
- እያንዳንዱ ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች መገንዘብ የሚችሉ፣ ተሰጥዖአቸውን የሚያበረታቱ እና በራስ-መተማመናቸውን የሚያበለጽጉ።
- በትምህርት ዓይነቱ ዝርዝር ውስጥ ብቃት-ያለው እውቀትን የሚያሳዩ እና ይህንኑም ከተማሪዎች ጋር በተሳካ-ሁኔታ ማጋራት የሚችሉ።
- ከስራ-ባልደረቦቻቸው ጋር እና ከማህበረሰቡ ጋር፣ ትብብርን የሚያሳድጉ።
- የላቀ-አመራርን የሚያሳዩ።
- በ2022-23 የትምህርት ዓመት ውስጥ፤ የማስተማር የስራ-ምድብ ሆነውን የስራ-ድርሻቸውን የጠበቁ።

ለ'Washington Post' የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ መምህር ሽልማት፣ ብቁ ለመሆን፤ እጩ-የሚሆኑት የሙሉ-ሰዓት (full-time) ርዕሰ መምህራን መሆን (ከቅድመ-መዋዕለሕፃናት እስከ 12ኛ)፤ እና እንደ ጋዜጣው ዝርዝር ግዛቶች መሠረት፤ እውቅናን-ካገኘ የዋሽንግተን ሜትሮ-አካባቢ ክልልው ውስጥ ከሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ መሆን አለባቸው። እጩዎቹ፤ እንደ ርዕሰ መምህርነት ቢያንስ - የ5 ዓመታት ልምድ ያላቸው፤ ከእነዚህም ዓመታት ውስጥ ሦስቱ፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም አሁን በሚያገለግሉበት የትምህርት ቤት ስርዓት ውስጥ፤ ያላቸው መሆን አለበት።

እጩዎቹ፤ ለ2022-23 የትምህርት ዓመት በአስተዳደርነት ማገልገል ያለባቸው እና የሚከተሉትንም መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው:

- በብቃት ማስተዳደር የሚችሉ።
- የፈጠራ-አስተሳሰብ እና ፈጠራዊ-ስራን የሚያበረታቱ እና የሚያሳዩ።
- በትምህርት ቤት እና በማህበረሰቡ መካከል ትብብርን የሚያሳድጉ።
- በተማሪዎች እና በወላጆች መካከል እንዲሁም በተቋሙ እና በሠራተኛው መካከል፣ ቀጣይነት ያለው ውይይትን የሚያስጠብቁ።
- በትምህርት አሰጣጥ መስኮች ውስጥ፣ ዘላቂነት ያለው እድገቶችን የሚጠብቁ።
- የቡድናዊ-አሰራር እንዲኖር የሚያበረታቱ።
- አመራርነትን የሚያሳዩ እና ትጋትን በምሳሌነት የሚያሳዩ።
- በመማሪያ-ክፍል ውስጥ፣ ቀጣይነት ያለው ንቁ ሚናን የሚጫወቱ።
- በ2022-23 የትምህርት ዓመት ውስጥ፤ እንደ ርዕሰ መምህር ሆነው የስራ-ድርሻቸውን የጠበቁ።

የACPS የዓመቱ ምርጥ ርዕሰ መምህር እና የዓመቱ ምርጥ አስተማሪ፤ በACPS ፓናል (panel) አማካኝነት፣ በ2023 መጀመሪያ ላይ የሚመረጡ እና በኤፕሪል (April) 2022 ላይ ደግሞ ማንነታቸው የሚገለጽ ይሆናል። ለ'The Washington Post ሽልማቶች'፣ እንደ ወደ የመጨረሻ-ዙር የደረሱ ሆነው፤ አሸናፊዎቹን በኤፕሪል (April) ወር 2023 ውስጥ ይታወቃሉ።

# ‘ACPS’ በአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ - የማስታወሻ ፕሮጀክት ፒልግሪሚጅ (Remembrance Project Pilgrimage)



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ ከኦክቶበር (Oct.) 6-10 ቀን 2022 - በሞትጎመሪ (Montgomery, AL) ውስጥ - ለ‘pilgrimage to the Equal Justice Initiative’s National Memorial for Peace and Justice and Legacy Museum’ ውስጥ በሚገባ-ተወክሎ ነበር። ለዚህ ብሄራዊ መታሰቢያ እንደ-አንዱ የታሪኩ አካል ሆኖ - ቦታውን በአሌክሳንድርያ ከተማ ውስጥ - የአካባቢ የግድያ ሰለባ-የሆኑትን ለማክበር-ፒልግሪሚጁ (pilgrimage) ክብር-ሰጥቷል። የአሌክሳንድርያ ማህበረሰብ የማስታወሻነት ፕሮጀክት (The Alexandria Community Remembrance Project (ACRP) - የሁለት የታወቁ የአሌክሳድርያ የግድያ ሰለባዎች የሆኑት - ጆሴፍ ማክ ኮሪ (Joseph McCoy)ን በ1897 እና ቤንጃሚን ታመስ (Benjamin Thomas)ን በ1899 ላይ የሞቱትን፤ ለማስታወስ የአፈር መሰብሰብ - በምሳሌያዊ ሁኔታ ለማንጸባረቅ ተሰጥቷል።

የአሌክሳንድርያ ከተማ ፒልግሪሚጅ - ተመራጭ-ሹማሙንቶችን፣ በACPS አመራርነቶች፣ ሠራተኞች እና ተማሪዎችን የተካተተ ነው። የACPS ሠራተኞች፣ ወደ ሞትጎመሪ (Montgomery) የተጓዙት፤ ይህ ተሞክሮ - በታሪኩ ላይ የተፈጠረውን ጎጂ-ህመምን ለማንጸባረ እና የመነጋገሪያ ነጥቦችን ለመክፈት - በተለይ-ደግሞ በዚህ ተሞክሮ በከፊል በዚህ ተሞክሮ ውስጥ ያለፉትን ተማሪዎች የሚረዳ-ነው። “የዘር ጥላቻ በጣም የተስፋፋ-የነበር መሆኑን ማሰብ በጣም-አሳዛኝ ነበር፣” ብለዋል የአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School (ACHS) - የአፍሪካን አሜሪካውያን የጥናት አስተማሪ ራአሊም ሻባዝ (RaAlim Shabazz)። “ትርጉም-የለሽ በሆኑ ምክንያቶች ተገድለው-የነበሩ ሰዎችን በማሰብ ብዙዎች ሲያነቡ ነበር።”

በጉብኙቱ ወቅት፤ ‘ACRP’ -የስድስት-ጫማ ርዝመት ያለውን የብረት-ዘንግ - ከ‘Memorial for Peace and Justice’ - በሁለቱም የአሌክሳንድርያ ሰለባዎች ስሞቻቸው የተቀረጸውን ለማግኘት-ተችሎ ነበር። መታሰቢያው በመግለጫነት ያቀረበው፤ ከ800 በላይ የብረት-ዘንጎች (steel pillars) - እያንዳንዳቸው፣ የ ‘Equal Justice Initiative’ በማረጋገጥ የካውንቲውን ስም የሚወክል እና በዚህ-ላይ ጥቃት-የደረሰባቸውን ስሞች በእያንዳንዱ ላይ ተቀርጾ የሚገኝ-ነው። በመታሰቢያው የሚገኙት ዘንጎቹ (pillars)፤ ከፍተኛ-ኃይል ያላቸው እይታዎች የሆኑ እና መጠን-የሌለው ውጤትን የሚያስገኙ ነበሩ፤ ብለዋል የACHS - የቲቪ እና የሚዲያ አቀራረብ አስተማሪ - ቤን ሊዮን (Ben Lyon)። በመጨመርም-ሲናገሩ፤ በየቦታ ስትመለከቱ - ከብረት ዘንጎች (steel pillars) ጋር የሰለባዎቹን ስሞች፣ ካንውንቲዎች፣ ስቴቶች፣ እና እነዚህ ድርጊቶች የተፈጸመባቸውን ከተማዎች - መዝግበው የያዙ፣ ተመሣሣይ ቅርጽ ያላቸውን መመልከት ይቻላል።

ከፒልግሪሚጁ አስቀድሞ፣ የጄፈርሰን-ሂውስተን (Jefferson - Houston) ከPreK-8 IB ትምህርት ቤት - የቴክኖሎጂ ኢንጂነሪንግ አስተማሪ - ኒኮል ሬዲንገር (Nicole Reidinger) - የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎችን - በACRP ወደ አላባማ መታሰቢያ (Alabama memorial) አፈርን ለማጓጓዥ ጥቅም-ላይ የዋሉትን መርከቦች ለመገንባት ተሣታፊ ለመሆን ጥያቄውን ተቀብለዋል።

ይህ ፒልግሪሚጅ (pilgrimage) በተጨማሪ ያካተተው፤ ወደ ሞትጎመሪ (Montgomery) እና ሴልማ (Selma) የሲቪል ራይትስ ቦታዎች እና ሚውዚየሞችን መጎብኘትንም ጭምር-ነበር። ከACPS ቡድን ውስጥ ከነበሩት-መካከል፤ ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ

ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ - ምክትል ሊቀ-መንበር ያሲንታ ግሪኔ (Jacinta Greene)፣ የትምህርት ቤት የቦርድ አባል - ኬሊ ካርማርክል ቡዝ (Kelly Carmichael Booz) እና ‘ACHS’ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች ተወካዮች - ነበሩበት።

የነበረውን-ተሞክሮ ወደፊት ለመመልከት እንዲቻል - ፒልግሪሚጁ (pilgrimage) በACHS ተማሪዎች ተቀድቶ-ነበር። ሊዮን (Lyon) እንዳለው፤ ተማሪዎቹ - የ25 ሰዓት የቪዲዮ ቀረፃን የቀዱት እና በተቀዳው ፊልም ላይ በጉዞው ላይ የነበሩ አስተማሪዎች እና ተማሪዎች ሃሳባቸውን እንዲሰጡ አጋርተዋል። “ይህን ከተመልከታችሁ በኋላ  - እንዴት ሕይወታችሁን እንደምትኖሩ - ተጽዕኖ ላያደርግ የሚችልበት ምንም-መንገድ የለም፣” ብለዋል ሊዮን (Lyon) - በነበራቸው ተሞክሮ ላይ ምልከታ-ሲያደርጉ።

የ‘ACHS’ ተማሪ እና የጥቁት ተማሪ ኅብረት (Black Student Union) አባል፤ አሜል ሞህዲል (Amel Mohdali) - ማንነቷል ላመግኘት በነበራት-ፍለጋ፤ በተሞክሮው ልብን-የሚነካ ስለነበረ - በተናገረችው መሠረት፤ “የቀደሙ-አባቶቻችንን (ancestors) ለማስታወስ - የላቀ-ደረጃ ለመድረስ እና እራስን-ለማሻሻል የሚተጉ ለውጥ-አምጪ ወኪሎች-እንሁን።” ብላለች። ሻባዝ (Shabazz) በመጨመርም፤ “ይህን ታሪክ ለመረዳት - ከፍተኛ የሆነ ህመም-ተሰምቶን የነበረ ቢሆንም፣ ከዚህ ተሞክሮ ጋር አብሮ ተያይዞ የሚመጣ ከፍተኛ መጠን ያለው ዕድገት (growth) እንደሚኖር አስባለሁ።” ብለዋል።

## የACPS፣ የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human resources) - ሬኔ ፓስካል (Rene Paschal)ን እንደ - የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human resources) ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር



የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) - የሬኔ ፓስካል (Rene Paschal)ን እንደ የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human resources) ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር አድርጎ - ከኦክቶበር (Oct.) 24 ቀን 2022 ጀምሮ መሾሙን ሲያሳውቅ-ደስታ ይሰማዋል። ፓስካል (Paschal)፤ ከዚህ ቀደም -  ርዕሰ መምህር ሆነው በሣሙዔል ተከር (Samuel W. Tucker ) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ - ከ2011 እስከ 2022 ድረስ አገልግለዋል። እንደ የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human resources) ተጠባባቂ ዋና ዳይሬክተር በመሆን፤ ፓስካል (Paschal) - የመምሪያውን ትግበራዎችን ለተቀጣሪ-ሠራተኞች ተሳትፎ እና ግንኙነቶች፣ ለማካካሻዎች እና ጥቅማ-ጥቅሞች፣ እና የሠራተኛ ቅጥርን-በመተግበር ላይ፣ ከሲኒየር አመራሮች ጋር እና ከትምህርት ቤት አስተዳደሮች ጋር በቅርበት የሚሰሩ-ይሆናል።

በአመራርነት ችሎታው በሚገባ-የታወቀው - ፓስካል (Paschal)፤ በሕዝት ትምህርት-አሰጣጥ ውስጥ በአርባኛዎቹ አመት የአገልግሎት ዘመኑ ውስጥ የሚገኝ ነው። የሦስተኛ፣ አራተኛ፣ እና አምስተኛ ክፍሎችን ያስተማረ ሲሆን፤ እንደ ትምህርት ቤት ካውስለር ሆኖ ያገለገለ እና እንደ የትምህርት ቤት ርዕሰ-መምህርነት ከ25 ዓመታት በላይ የአመራርነት-ብቃት አለው። በተከር (Tucker) ውስጥ፣ የ‘U.S. Department of Education’ንን - የ‘21st Century Community Learning Centers’ የገንዘብ-

እርዳታን - የተማሪዎችን የቀለም-ትምህርት ስኬታማነት እና ደህንነትን ለማስጠበቅ በሚካሄደው - ለ'ከትምህርት ቤት በኋላ ፕሮግራም (after-school program̈)' አስገኝቷል። በ2021-22 ውስጥ፣ ፓስካል (Paschal)፣ የ'National Distinguished Principal' ሽልማትን - በቨርጅኒያ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት የርዕሰ-መምህራን ማኅበር (Virginia Association of Elementary School Principals (VAESP) በማግኘት-ተሸልሟል። ይህ የሽልማት ፕሮግራም፤ ርዕሰ-መምህራኖችን - ከፍተኛ ደረጃዎችን ለትምህርት አሰጣጡ፣ ለተማሪ ውጤታማነት፣ የተማሪዎችን ፀባይ እና የአሰራር ሁኔታ፣ ቤተሰቦች እና ሠራተኞችን በመማሪያ-ማህበረሰባቸው ውስጥ እውቅና-የሚሰጥ እና የሚያከብር-ነው።

ከዚህ-ቀደም የነበረው ክፍል-አቀፍ የሆነ (division-wide) ልምድን - እንደ በሙያ-ስልጠና መማር ዳይሬክተርነት፣ የስራ-መስክ መሰል እና የትምህርታዊ ቴክኖሎጂን - በሌላ የትምህርት ቤት ክፍል/division ውስጥ መስራትን ጨምሮ - ወደ ACPS ከመምጣታቸው-በፊት አገልግለዋል። ፓስካል (Paschal)፤ በዚህ የተጠባባዊ የስራ-ድርሻ ላይ - የሰው-ልጅ የመገኛ ምንጮች (Human resources) - ቋሚ ዋና ዳይሬክተር - ለትምህርት ቤቱ ክፍል እስከሚለይ ድረስ ያገለግላል። ፓስካል (Paschal)፣ የባችለር ዲግሪያቸውን በትምህርት/Education - ከኬንት ስቴት ዩኒቨርስቲ (Kent State University) ያገኙ፣ እና የማስተርስ የትምህርት ዲግሪያቸውን ደግሞ በማማከር (counseling) - ከአሪዞና-ዩኒቨርስቲ አግኝተዋል።

## ስለ APCS FY 2024 የበጀት ሂደት እወቁ: አክቶበር (Oct.) 17 ቀን 2022 - የማህበረሰብ ፎረም የሚቀዳ (Recording)




የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የበጀት-ዓመት 2024 የተቀናጀ የገንዘብ-እርዳታ በጀት (Combined Funds Budget)ን ማካሄጃ ሂደቱን አስጀምሯል። በአክቶበር (Oct.) 17 ቀን 2022 የተደረገው የማህበረሰብ የበጀት ክፍለጊዜ፤ ስለ በጀት ሂደቱ፣ ስለጊዜ-አቀማመጡ ለማወቅ ዕድል የሰጠ እና፣ የዓመታዊ የበጀት አስቸጋሪ ፈታኝ የሆኑበትን ችግሮችን፤ ክፍሉ በዚህ ሂደት ወቅት ምላሽ-እንዲሰጥበት አቅርቧል። የዚህ የማህበረሰብ የበጀት ፎረም - በአምስት ቋንቋቆች ተቀድቶ-የሚገኝ ይሆናል። በACPS Fiscal Year 2024 (FY) የተቀናጀ የገንዘብ-እርዳታ በጀት (Combined Funds Budget) እና በFY 2024-33 የካፒታል ማሻሻያ ዕቅዶች (Capital Improvement Plans (CIP) በጀት ላይ፤ እባካችሁ፤ መረጃዎችን አግኝታችሁ ቆዩ እና በማደራጀቱ ሂደት ላይ ተሣታፊ-ሁኑ። በሂደቱ ውስጥ ቀጣዩ-እርምጃ የሚሆነው፣ የጠቅላይ-ስራ አስኪያጁ ሃሳብ-የቀረበበትን የFY 2024-33 CIP በጀትን - በኖቬምበር (Nov.) 10 ቀን 2022 በሚደረግው የትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ማቅረብ ይሆናል።

## በቅርቡ-የሚከናወን: ‘PTAC’፣ ‘PSAS’ እና ‘ACPS’፣ የሕዝብ ደህንነት ጥበቃ ፎረም - በኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 እንዲደረግ፣ ተዘጋጅቷል



የአሌክሳንድርያ የፒቲኤ (PTA) ካውንስል (The Alexandria PTA Council (PTAC)፤ ወላጆች ደህንነቱ-ለተጠበቀ የአሌክሳንድርያ ትምህርት ቤት (Parents for Safe Alexandria Schools (PSAS)፣ እና የአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS)፤ የሕዝብ የደህንነት-ጥበቃ ፎረምን - በኦክቶበር (Oct.) 26 ቀን 2022 ላይ የሚያዘጋጁ-ይሆናል። በዚህ ፎረም ወቅት፤ ተሳታፊዎች ስለ ተማሪዎቻችንን እና ሠራተኞችን በደህንነት ስለመጠበቅ እንዲረዳ - ሁላችንም ምን ማድረግ እንዳለብን ለፓናል የማህበረሰብ ባለሞያተኞች ጥያቄ ለማቅረብ ዕድል ይሰጣል።

ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የሆኑት - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፤ በትምህርት ቤቶቻችን እና በማህበረሰባችን ውስጥ፣ የደህንነት-ጥበቃን ጠብቆ-በመገኘት ላይ - የክፍሉ/divisionን - ከአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ (Alexandria Police Department (APD) ጋር የሚያደርገውን ትብብር፣ እና በዚህ የጋራ-በሆነ ዓላማ ላይ ቤተሰቦች ከACPS-ጋር እንዴት እንደሚሠሩ፤ ንግግር-ያደርጋሉ። ልጅ-ቢሰማው አስቸጋሪ-ሊሆን የሚችል (Child-sensitive) ይዘት፤ ውይይት-እንደሚደረግበት፤ እባካችሁ አስታውሱ። የፎረሙ ፓናሊስቶች (Panelists) ሆነው የተካተቱት:

- የACPS የደህንነት እና የጥበቃ አገልግሎቶች (Safety & Security Services) ዳይሬክተር — ጆን ኬንትሬራስ (John Contreras)።
- የACPS የትምህርት ቤት የማህበራዊ ስራ ዳይሬክተር — ፋይዛ ጃክሰን (Faiza Jackson)።
- የአሌክሳንድሪያ የፖሊስ መምሪያ ሹም — ሪቻርድ ሳንዳቮል (Richard Sandavol)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ የወንበዴ-ቡድን (Gang) መከላከያ የማህበረሰብ ታስክ-ፎርስ (Task Force) አባል — ማይክ ማኪይ (Mike Mackey)።
- የ‘Be SMART’ የጦር-መሣሪያ (Gun) በጥብቅ-ቦታ ማስቀመጥ (Secure Gun Storage) ፕሮግራም፤ የእያንዳዱ-ከተማ የጦር-መሣሪያ (Gun) የደህንነት-ጥበቃ — አንዲ ኮርሶ (Andy Corso)።
- የአሌክሳንድርያ ከተማ፣ የመጓጓዣመምሪያ (Department of Transportation) & የአካባቢያዊ አገልግሎቶች (Environmental Services) — አሌክስ ካሮል (Alex Carroll)።

የትምህርት ቤት የደህንነት-ጥበቃ ፎረም፣ በጆርጅ ዋሽንግተን መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት - የመሰብሰቢያ-አዳራሽ ውስጥ፣ ከ6:30 እስከ 8 p.m ድረስ ይካሄዳል። ፒዛ (Pizza)ም፣ ይቀርባል። በhttps://acps.cc/SafetyForum ላይ፣ ቤተሰቦች መገኘታቸውን-እንዲያረጋግጡልን (RSVP እንዲያደርጉ) እንጠይቃለን። መላው-ሕዝቡም፣ በዙም (Zoom) አማካኝነት፣ በhttps://acps.cc/psfonzoom ላይ - በደህንነት-ጥበቃው ፎረም ላይ መካፈል ይችላሉ። የማስተርጎም አገልግሎቶች፤ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ በዳሪ፣ እና በስፓኒሽ ቋንቋዎች - ለሁለቱም በአካል-ተገኝቶ ለሚደረገው እና ለርቀት (virtual) ዝግጅቶቹ - መገኘት የሚችል-ይሆናል። ተጨማሪ-ለማወቅ - የየዝግጅቱን ድህረ-ገጽ በመጎብኘት፤ ወይም ተለጣፊ-ማስታወቂያዎቹን፤ በእንግሊዘኛ፣ በስፓኒሽ፣ በአማርኛ፣ በአረብኛ፣ እና በዳሪ - በመመልከት-ማወቅ ይቻላል።

## ቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week)፣ ከዕፅ-ነፃ የሆነ አኗኗርን፤ አክብሯል




የቀይ-ሪባን ዘመቻ (The Red Ribbon Campaign) በሚሊዮኖች የሚቆጠሩትን - በሃገሪቱ ዙሪያ የሚገኙ ወጣት ታዳጊዎችን - ከኦክቶበር 23-31 ድረስ የRed Ribbon Week ስለሚያከብር፤ ለሁሉም ዜናውን ለማሰራጨት ይፈልጋል። የ2022 የቀይ-ሪባን (Red Ribbon) መገለጫው/theme ሆኖ የቀረበው፤ በሃገሪቱ - በብሄራዊ-ደረጃ፣ ረጅም-ዕድሜ ያስቆጠረው እና ትልቁ የዕፅ መከላከያ ፕሮግራም - የሆነው፤ "Celebrate Life: Live Drug Free." ነው። የቤተሰብ እና የማህበረሰብ ተሣትፎ (The Family and Community Engagement (FACE) ማዕከል - በአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ውስጥ - ከበርካታ በአጋርነት ከሚሠሩ ጋር አሁንም ተመልሰው በቀይ-ሪባን ዘመቻ በአሌክሳንድርያ (Red Ribbon Campaign in Alexandria) ውስጥ በመሆን: የአሌክሳንድርያ የአደንዛዥ ዕፅ መከላከያ ቅንጅት (Substance Abuse Prevention Coalition of Alexandria (SAPCA)፣ የአሌክሳንድርያ ከተማ የማህበረሰብ እና የሰብዓዊ አገልግሎቶች መምሪያ (Department of Community and Human Services (DCHS)፣ የኖርዘን-ቨርጅኒያ - የልጅ-ጥቃትን አሁን አቁሙ (Stop Child Abuse Now (SCAN)፣ እና የከንቲባው ዘመቻ የሆነውን ማንጓጠጥን እስከመጨረሻው ማጥፋት (End Bullying) ውስጥ፤ ኃይላቸውን አስተባብረው ይካፈላሉ።

የቀይ-ሪባን ሣምንት (A Red Ribbon Week) አዋጅ - ባለፈው የውድድሩ አሸናፊ ከሆኑት ጋር እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በአሌክሳንድርያ ከተማ ካውንስል ስብሰባ በሆነው - ማክሰኞ፣ አክቶበር (Oct.) 25 ቀን 2022 ላይ የሚነበብ-ይሆናል። ለተሰብሳቢው ንግግር ለማድረግ፣ የACPS ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) የሚገኙ ይሆናል።

ይህ የቀይ-ሪባን ዘመቻ (Red Ribbon Campaign) - ማህበረሰቡ አብሮ-በአንድነት ለመቆም-እንዲችል እና በጉልህ-በሚታይ ሁኔታ ዕፆችን በመቃወም-በመቆም፤ - ከታዳጊዎች ጋር ግንኙነትን መፍጠር-የሚያስችል፤ ውጤታማ የሆነ መንገድ ነው። በተለይ-ደግሞ በዚህ የኦፒኦይድስ (opioids) የታዳጊ-ወጣት ተጠቃሚዎች እና የፈንተኖል (fentanyl) አደጋ-ባንዣበበት - በዚህ ወቅት ደግሞ የበለጠ-ጠቃሚ ነው።

ሁሉም የ'ACPS' ተማሪዎች፣ ከዕፅ ነፃ የሆነ የአኗኗር-ሁኔታን ለማበረታታት እና ፖስተሮችን ከሦስቱ ምድቦች ውስጥ-በአንዱ ለማስገባ: መጀመሪያ-ደረጃ (elementary)፣ መካከለኛ-ደረጃ ትምህርት ቤት (middle school) እና ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (high school) አስገብቶ - በሬድ ሪባን (Red Ribbon) የፖስተር ውድድር ውስጥ እንዲካፈሉ ይጋብዛል። ሁሉም ፖስተሮች፤ እስከ ኖቬምበር (Nov.) 15 ቀን 2022 ድረስ መግባት-አለባቸው፤ ወይም በዚህ-ቀን ፖስታ-የተላከበት ምልክት ኖሮት-በሚከተለው አድራሻ መላክ አለበት:

Ms. Daniela Perez-Bravo
ACPS Central Office at
1340 Braddock Pl, 5th Floor,
Alexandria, VA 22214

የኤሌክትሮኒክ ስሪቶቹ (Electronic versions)፤ ወደ face@acps.k12.va.us ወይም በwww.acps.cc/RRWposter22 ሊገቡ-ይችላሉ።.

ከዕፅ-ነፃ የሆነ የአኗኗር-ዘዴን የሚያበረታታ፤ በሰዓሊነት አቀራረብ እና በጠንካራ መልዕክት አቀራረባቸው ላይ መሠረት አድርጎ፤ ሦስት አሸናፊ የሆኑ ፖስተሮች ይመረጣሉ። የ'Red Ribbon poster' ውድድር አሸናፊዎች፤ እያንዳንዳቸው የ$100 የስጦታ ካርድ (gift card) የሚያገኙ፣ እና የሰሩትም ፖስተር - በ2023 የቀይ-ሪባን ሣምንት 2023 (Red Ribbon Week 2023) ወቅት-ውስጥ እንዲታይላቸው ይደረጋል።

ባለፈው-ዓመት፤ ACPS - በቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) እንቅስቃሴዎች ላይ በነበሩት በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተሳትፎ ላይ፣ ከ175 በላይ የፖስተር ውድድር ገብተው - ግሩም-የሆነ ምላሽ-አግኝቶ ነበር። በዚህ የቀይ-ሪባን ሣምንት (Red Ribbon Week) ወቅት የፖስተር ዲዛይናቸው የሚቅርብላቸው አሸናፊ ተማሪዎች የሚከተሉት ናቸው።

- አሽሊ ኢዛቤል ሉና ይሜኔዝ (Ashly Isabel Luna Jimenez) - የአንደኛ-ክፍል ተማሪ በዊሊያም ራምዚ (William Ramsay) የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት
- ካይትሊን ፊህሊ (Caitlin Feehely) የ12 ክፍት ተማሪ፣ በአሌክሳንድርያ ከተማ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (Alexandria City High School)

## የኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 - የትምህርት ቤት ቦርድ ማጠቃለያ



በዚህ ኦክቶበር (Oct.) 20 ቀን 2022 ስብሰባው ላይ፤ የትምህርት ቤት ቦርዱ፣ የሚከተሉትን ርዕሶች ላይ ተነጋግሮበታል:

- በቅጥር (Recruitment) ላይ፣ አዲስና ማሻሻያ (Recruitment Update)
- የ'FY22' የ4ተኛው አጋማሽ (Quarter) እና የ'FY23' የ1ኛ አጋማሽ (Quarter)፤ የካፒታል የማሻሻያ-ፕሮጀት (Capital Improvement Projects (CIP) ሪፖርት
- የ'CIP' እንደገና-ከለሳ የተደረገበት የሦስት-ወር (Quarterly) ሪፖርት

የትምህርት ቤት የቦርድ ስብሰባ አጀንዳዎችን እና ሰነዶችን ለማግኘት፤ Electronic School Boardን ይጎብኙ። ስብሰባዎችን በቀጥታ ለመመልከት እና ለመካፈል እንዴት እንደሚችሉ መረጃዎችን ለማግኘትም፤ በትምህርት ቤት ቦርድ ስብሰባ ድህረ-ገጽ መጎብኘት ትችላላችሁ።

# በኦክቶበር (Oct.) 13 ቀን 2022 - COVID-19 የአሌክሳንድርያ የCOVID-19 ማህበረሰብ ያለበት-ደረጃ




እስከ ኦክቶበር (Oct.) 13 ቀን 2022 - ባለው-ጊዜ፤ የአሌክሳንድርያ ከተማ የCOVID-19 ማህበረሰቡ-የሚገኝበት ደረጃ - ዝቅተኛ/low ሲሆን፤ ባለፉት ሰባት ቀናቶች ውስጥ፤ በየ100,000 ሰዎች፣ 72.13 ታማሚዎች አሉት። የበለጠ ለማወቅ፤ Alexandria COVID-19 dashboard ጎብኙ።

የመረጃ-ስብስቡ (data)፤ በመጨረሻ-እንዲስተካከል የተደረገው በኦክቶበር (Oct.) 13 ቀን 2022 ላይ እንደሆነ፣ እባካችሁ አስታውሱ። የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማዕከላት (Centers for Disease Control and Prevention)፤ በሦስት ሜትሪክስ (three metrics) ጥምሮች ውስጥ - የCOVID-19 የማህበረሰብ የደረጃ-መጠንን ለመወሰን ተመልክቷል: አዲስ የCOVID-19 ታማሚ ሆነው የተመረመሩበትን በ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ፤ ገብተው-የተኙ በCOVID-19 ታካሚዎች የተያዙ አልጋዎች - በእያንዳንዱ የCOVID-19 በሽተኛ-ቁጥር፤ እና አጠቃላይ አዲስ የCOVID-19 ታማሚዎችን በየ100,000 የሕዝብ-ቁጥር/population - በአለፉት ሰባት ቀናት ውስጥ ተመልክቷል።